መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቀራቢዎች



# ቤተክርስቲያን ችግር ገጠማት፡፡

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ ኃምሳ ቀናት በኋላ ፣ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ተከታዮች ውስጥ ለመኖር መጣ። ምንም እንኳን ደቀመዛሙርቱ እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዴት አንድ እንደሆኑ ባያውቁትም፣ አግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ እንደሆነ በማወቃቸው ደስተኞች ናቸው። ሐዋሪያቱ ስለ ኢየሱስ ለሌሎች እንዲናገሩ እግዚአብሔር አስደናቂን ነገር አድርጎላቸው ነበረ።



በኢየሱስ ያምኑ የነበሩ ሰዎች ያላቸውን ነገር
ሁሉ እርስ በርሳቸው ይከፋፈሉ ነበረ ፤
በዚህም ደሆችን ይንከባከቦቸው ነበረ፡፡ ነገር
ግን አንድ አናኒያ እና ሰጲራ የሚባሉ ባልና
ሚስቶች ታማኞች አልነበሩም፡፡
መሬታቸውን ሸጠው ያመጡት
ገንዘብ በሺያጩ ያገኙትን
ሁሉ እንደሆነ አስመስለው
አቀረቡት፡፡
በሚስጥርም ፤
ለራሳቸው አስቀሩ፡፡





“መንፈስ ቅዱስ ትዋሽ ዘንድ ሰይጣን
እንዴት ልባችሁን በክፋት ሞላ;” ብሎ
ጴጥሮስ አናኒያን ጠየቀው፡፡
“እግዚአብሔርን እንጂ ፣ሰውን
አላሳታችሁም፡፡” አናንያም ወደቀ ፤
ትንፋሹም ተቋረጠ፡፡ አንድ ጎበዝም
ሰበሰበው ፤ ወሰደውናም ቀበረው፡፡



ከጥቂት ሰዓታት በኋላም ፣ ሳጺራ ገባች ፤ ባልዋ እንደሞተ አላወቀችም ነበረ፡፡ እርሷም ስለ ገንዘቡ ዋሸታ ነበረ - በእርሷ ላይም ተመሳሳይ ነገር ሆነባት፡፡ ይሔንንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነባቸው፡፡



እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ
ብዙ ድንቅና ተዓምራትን
በሐዋሪያቱ በኩል አደረገ።
ለምሳሌ ፣ የጴጥሮስ
ጥላ ሲነካቸው የታመሙ
ሰዎች ይፈወሱ ነበረ።



የእግዚአብሔር መገኘት
የሚታይበት ፣ የታላላቅ
ተዓምራቶች ጊዜ ነበረ፡፡
እጅግ ብዙ ሰዎች
በኢየሱስ ያምኑ ነበረ፡፡
ይሔም ሊቀ ካህኑን
ያበሳጨው ነበረ፡፡ እርሱም ፣
ሐዋሪያቱን በወሕኒ ውስጥ
ያኖራቸው ነበረ፡፡





ነገር ግን በምሽት ፣
የእግዚአብሔር መልዓክ
የወሕኒውን በር ከፍቶ
ወደ ውጪ አወጣቸውና
፣ እንዲህ አለ ፣ “ሒዱ ፣
በመቅደስ ቁሙና ፣
የዚህን የሕይወት ቃል
ለሕዝቡ ሁሉ ተናገሩ፡፡”
ሐዋሪያቱም ወጡና ስለ
ኢየሱስ መናገር ጀመሩ፡፡
በጠዋትም ፣ የሊቀ
ካሕናቱ ሰዎች ወሕኒ ቤቱ
ባዶ መሆኑን አወቁ፡፡

በሌላም ጊዜ ሲያገኛቸው ፣ ሊቀካሕናቱ ሐዋሪያቱን ተቆጣቸው ፤ “በዚህ ስም አትናገሩ ብለውን አላዘዝናችሁምን;” ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋሪያትም ፣ “ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ  አለብን፡፡” ብለው መለሱ፡፡

ሊቀካሕናቱም እጅግ ጨካኝ ነበረና ፣ ሐዋሪያቱን ሊገድላቸው አሰበ፡፡

በምትኩም ፣ እንዲገረፉና እንዲለቀቁ ብሎ አዘዘ፡፡

ሕመማቸው እያለም ፣

እግዚአብሔርን ታዝዘው

ስለ ኢየሱስ መስበካቸውን

ቀጠሉ፡፡



አንድ ቀን እስጢፋኖስ የሚባል ሰው ታሰረ ፡፡ እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስን ይወደዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስም እርሱን ስለ ኢየሱስ እንዲናገር ይጠቀመው ነበረ፡፡ እስጢፋኖስ እግዚአብሔርን እየተሳደበ ነው ብለው አንዳንድ ሰዎች ዋሹ፡፡ ብዙ ካፌዙበት በኋላ ፣ እስጢፋኖስ ኢየሱስ ላይ ስላለው እምነት በድንጋይ ተወግሮ ሞተ፡፡



ከመሞቱ አስቀድሞ ፣ እስጢፋኖስ ፣ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ፣ ወደ ሰማይ
ትኩር ብሎ የእግዚአብሔረን ክብርና ኢየሱስ
ክርስቶስን በቀኙ ሆኖ ተመለከተ፡፡



ሕዝቡ እስጢፋኖስ ወደ
እግዚአብሔር እየተጣራ ፣
“ጌታ ኢየሱስ ፣ መንፈሴን
ተቀበል፡፡” ሲል በድንጋይ
ይወግሩት ነበረ፡፡
ከዚያም ፣ ኢየሱስ
በመስቀል ላይ እንዳለው ፣
ይሔም ጠቢብ ሰው
በመጨረሻው እስትንፋስ
ውስጥ እያለ ለገዳዮቹ
ምሕረትን ይለምን ነበረ፡፡

የእስጢፋኖስ ሞት አዲስ የስደት ማዕበልን ቀሰቀሰ ፡፡ ሳውል የሚባል ወጣት ፣ ከእስጢፋኖስ ገዳዮችጋ ይተባበር የነበረ ፣ ያገኘውን ክርስቲያን ሁሉ ያስር ነበረ፡፡ ብዙዎቹም ከቦታቸው ተባርረው ፣ በይሁዳና በሰማሪያ ተበተኑ፡፡ ሐዋሪያቱ ብቻ በኢየሩሳሌም ውስጥ ቀሩ፡፡



ምንም እንኳን ጠላቶቻቸው ሊገድሏቸው ቢሞክሩም ፣ የተበተኑትም ስለ ኢየሱስ የሆነውን መልካሙን ዜና በሁሉ ስፍራ ይሰብኩ ነበረ፡፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በእነርሱ ሆኖ ይሰራ ስለነበረ ፣ አንዳች ነገር የኢየሱስን ተከታዮች ሊየስቆማቸው አልቻለም፡፡



ቤተክርስቲያን ችግር ገጠማት፡፡

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሐዋሪያት ስራ 5-7

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16